የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: የካቲት 30 2015
ቁጥር/REF NO 1256/ቀ516/15

ለሁሉም የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች
ለሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች
ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
ባሉበት

ጉዳዩ፡- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊስ ስለመላክ፡፡

የኢፌዲሪ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረገው 17ኛው መደበኛ ስብሰባ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ላይ በመወያየት አጽድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ወስኗል፡፡

በዚሁ መሠረት በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪነት 28 ገጽ የፖሊሲውን የአማርኛ ቅጅ አንድ ጥራዝ አያይዘን የላክን መሆኑን እያስታወቅሁ፤ ከፀደቀበት ከየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

እንዲያውቁት
ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ግልባጭ፡-
ለሚኒስትር ጽ/ቤት
ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [አጠቃላይ ትምህርት ልማት ዘርፍ]
ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ]
ትምህርት ሚኒስቴር፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

የካቲት 2015

አዲስ አበባ

# ማውጫ


1. መግቢያ ..... 1
2. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መነሻዎች ..... 2
3. የፖሊሲው አስፈላጊነት እና ዓላማዎች ..... 4
4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ..... 7
5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች ..... 15
6. ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን ..... 17
7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 17
8. ተዛማጅ ፖሊሲዎች ..... 21
9. መሠረታዊ የቃላት ፍቺ ..... 23

## 1. መግቢያ

የአንድን ሀገር እድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ፣ በዜጎች መካከል ያለን እምነት እና መልካም ግንኙነት ለማዳበር እንዲሁም የሕግ የበላይነትንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ትምህርትና ሥልጠና ወሳኝ ሚና አላቸው። ይህን ውጤት ለማስመዝገብ የትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ከኢኮኖሚና ከማሕበራዊ እድገት ጋር በጥብቅ ተሳስሮ መተግበር ይኖርበታል። ከዚህ መርህ አኳያ ትምህርትና ሥልጠናን ከልማት ጋር በማስተሳሰር የሀገራችንን እድገት ለማፋጠን እንዲቻል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም. ተቀርጾ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። በዚህ ፖሊሲ መሠረት ባለፉት ሃያ ስምንት ዓመታት በየአምስት ዓመቱ የተከፋፈሉ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብሮች ሀገሪቱ ቃል ከገባችባቸው የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ጋር በማስተሳሰር ሲተገበሩ ቆይተዋል።

በዚህም መሠረት ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በማስፋፋት የትምህርትን ተደራሽነት ማሳደግ ተችሏል። በዚህም ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል በማቅረብ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም በሚፈለገው ጥራት እና ዓይነት ከማቅረብ አንጻር ክፍተቶች ነበሩበት። በተጨማሪም ሥርዓተ-ትምህርቱ ተግባር ተኮር ባለመሆኑ ሥራ ፈጣሪ የሆኑ ዜጎችን ከማፍራት፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎችን ከማበረታታት አንጻር እንዲሁም ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ በማድረግ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉት በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ተረጋግጧል።

ስለሆነም ፖሊሲው ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች፣ እጥረቶች እንዲሁም የዘርፉን ዓለም አቀፋዊ ለውጦችን መሠረት በማድረግ ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈልጓል። ይህ ፖሊሲ የትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ ያለበትን ደረጃ በመገምገም የዘርፉን ዋና ዋና ችግሮችና የነባሩ ፖሊሲ ማነቆዎች በአዲሱ ፖሊሲ የሚፈቱበትን አግባብ፣ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲው ተፈጻሚ ሲሆን የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶችን በሚያሳይ መልክ የተዘጋጀ ነው።

## 2. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መነሻዎች

ትምህርትና ሥልጠናን ከልማት ጋር በማስተሳሰር የሀገራችንን እድገት ለማፋጠን እንዲቻል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም. ተቀርጾ ሲተገበር ቆይቷል። ይህን ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በየአምስት ዓመቱ የተከፋፈሉ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብሮች ሀገሪቱ ቃል ከገባችባቸው የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱ ልማት ግቦች ጋር በማስተሳሰር ሲተገበሩ ቆይተዋል። በዚህም መሠረት በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ተደራሽነትንና ፍትሀዊነትን በማረጋገጥ በኩል ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም እድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ አሁንም ትምህርት ያልጀመሩ ሕጻናት መኖር፣ የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ችግሮች እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ያላቸው በተለይም የአካል ጉዳተኞችና የጐልማሶች የትምህርት ተሳትፎ መጠን ዝቅተኛ ነው። የትምህርት ጥራትም እያሽቆለቆለ የመጣ ሲሆን እንደ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው በየደረጃው ያሉ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን 50 በመቶና በላይ ውጤት ማምጣት አልቻሉም። ሥርዓተ-ትምህርቱም በንድፈ ሃሳብ የታጨቀ፣ ለነባራዊ የሀገሪቱ ሁኔታዎች ምላሽ የማይሰጥ፣ የሀገር በቀል እውቀትን ያላካተተ፣ በየጊዜው የማይፈተሽ፣ ዜጎችን በግብረገብና በመልካም ሥነ ምግባር በበቂ ሁኔታ ያላነፀ ከመሆኑም በላይ ለሥራ ፈጣሪነትና ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያዘጋጅ አልነበረም። መምህራንም ብቃትን ተላብሰው ተማሪዎችን በመረዳትና በመርዳት እንዲሁም ከሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ በማድረስ ረገድ ውስንነት ያለባቸው ሲሆን ትምህርት ቤቶችም ቢሆኑ ለመማር ምቹ ያልሆኑ፣ አስፈላጊው ግብዓት ያልተሟላላቸውና ትምህርቱንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አስደግፈው የሚሰጡ አይደሉም።

በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል ከማቅረብ አኳያ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በዓለም ደረጃ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረውና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስትራቴጂ ወጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ከፖሊሲ፣ ከስትራቴጂ፣ ከአደረጃጀትና ከአሠራር፣ ከአተገባበር እንዲሁም ከፋይናንስ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ኢኮኖሚውን በተለይም ግብርናውን ማዘመን አልተቻለም። ከስትራቴጂ አንጻር ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የሥልጠና ተቋማት አልተደራጁም። ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት ለሆነው ለእርሻና ግብርና ትኩረት ያልሰጠና ይህንን አዘምኖ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ሊደግፍ አልቻለም። የተለያዩ የኢንዱስትሪና የኢኮኖሚ ዘርፎች ተቀናጅተው ለዘርፋቸው ተገቢ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን

የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎች የሚያሠለጥኑበት ሥርዓት አልተዘረጋም። ሀገራዊ ፍላጎትን በትክክል ያገናዘበ የሙያ ደረጃ በማውጣትና የትብብር ሥልጠናን መተግበር የሚያስችል ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም።

የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን በማስፋት በኩል ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተቋማት የሚፈለገውን ስታንደርድ ያልጠበቁና ብዙ መሠረተ-ልማት ያልተሟላላቸው መሆኑ በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ ጥራትና አግባብነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣ ኢኮኖሚው ሳይፈቅድ በ70:30 ቀመር ላይ የተመሠረተው የሣይንስና የማህበራዊ ሣይንስ የትምህርትና ሥልጠና ምጥጥን መተግበሩ፣ በተግባር የተደገፈ ትምህርት አለመሰጠቱና ጠንካራ የሆነ የጥራትና አግባብነት ተቆጣጣሪ ባለመኖሩም ጥራቱንና አግባብነቱን ማስጠበቅ አልተቻለም። በሌላ በኩል ሲታይ ለጥራት ወሳኝ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ውስንነቶች ተስተውሏል። በአጠቃላይ ሲታይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰረና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ሥልጠና እውን ማድረግ አልቻሉም።

ከትምህርት አመራር አንፃር ስንመለከተው ከፌዴራል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ያለው አብዛኛው በየደረጃው ያለው የትምህርት መዋቅር የትምህርት አመራርና ባለሙያ ኃላፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የጐደለው በመሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን በአግባቡ በመምራት ለተሻለ ውጤት ያበቃ አልነበረም። ለዚህም ሙያዊ አቅም ያላቸውን በውድድር አለመመደብና ውጤታማነት የጐደለው የሥልጠና ሥርዓት የትምህርቱ ጥራት እያሽቆለቆለ እንዲመጣ አንዱ ምክንያት ሆኗል።

በተጨማሪም መንግሥት ባለፉት ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋፋት ከፍተኛ የሆነ ሀብትን በመመደብ የዘርፉ ዋነኛ የፋይናንስ ምንጭ ነበር። ይህ ተደራሽነትን በማስፋፋት በኩል አወንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ፋይናንስ ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል። በመሆኑም በቀጣይ አማራጭ የገቢ ምንጮችን እንዲሁም ፋይናንስ አደራረግ ሥርዓት ማስፈን ያስፈልጋል።

ዩኒቨርሲቲዎች የሚያፈሩትን የሰው ኃይል ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችላቸው የአካባቢያቸው ፀጋን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ላይ ሲሰማሩ እንደሆነ ቢታመንም በሀገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች

ሁሉንም የትምህርት ዓይነት በመክፈት ውጤታማ ያልሆነ የሀብት አጠቃቀም ተከስቷል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች ያላቸውን የተፈጥሮ ፀጋንና የተሰጣቸውን ጥራት ያለው የሰው ኃይል የማፍራት ተልዕኮ መሠረት ያደረገ ለመሠረተ ልማት ማስፋፋት እንዲሁም ለመማር ማስተማር ተግባራቸው ማስፈፀሚያ የሚውል የሀብት አመዳደብ ሥርዓት ሊበጅ ይገባዋል።

በመሆኑም አሁን እየተተገበረ ያለውን የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በመፈተሽ በሁሉም ዘርፎችና ደረጃዎች ለሚታዩት ነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥና ተወዳዳሪ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይገባል።

## 3. የፖሊሲው አስፈላጊነት እና ዓላማዎች

### 3.1 የፖሊሲው ማሻሻል አስፈላጊነት

በሥራ ላይ ያለውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ለመከለስ ያስፈለገበት መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓታችን በንድፈ ሀሳብ የታጨቀ እና ለተግባር ትምህርት ተገቢውን ትኩረት ያልሰጠ በመሆኑ፤
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰረና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ሥልጠና አለመሰጠቱና በዚህ መሠረት በቂና ተገቢ የሰው ኃይል አለመቅረቡ እና ሠልጥነው/ተመርቀው የወጡ ዜጎችም ሥራ ፈጣሪ ባለመሆናቸው፤
- እስካሁን ሲተገበር የቆየው ትምህርትና ሥልጠና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት መሠረት የሆኑት ሴክተሮች ሽግግርና ምርታማነትን ከማቀላጠፍ አንፃር ክፍተት የነበረበት በመሆኑ፤
- የኢኮኖሚ ዘርፎችና የትምህርትና ሥልጠና ሴክተር በሚዘጋጀው የሰው ሃይል ላይ በቅንጅት ባለመሥራታቸው፤
- ሀገራዊ ፍላጎትን በትክክል ያገናዘበ የሙያ ደረጃ በማውጣትና የትብብር ሥልጠናን መተግበር የሚያስችል ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሥርዓት ባለመዘርጋቱ፤

➢ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ የመጣውን ቴክኖሎጂና በእውቀት ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚያዊ ውድድር ላይ ውጤታማ የሚያደርግ የሰው ሀብት በማልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርግ ፖሊሲ መቅረፅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

➢ የሀገር በቀል ዕውቀት በሀገራዊ የሰው ኃይል ልማት ውስጥ በማካተት የሀገር በቀል እውቀቶች ከዘመናዊ እውቀት ጋር የተጣጣመ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በመቅረፅ ለሀገር ያላቸውን አስተዋጽኦ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

➢ በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የሚያፈሩት የሰው ሀብት ያላቸውን የተፈጥሮ ፀጋ እና ተልዕኮ መሠረት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን በመፈተሽ ማሻሻልና በሀገር ደረጃ የሚፈለገውን እድገትና ልማት ለማምጣት በሚያስችል መልክ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

## 3.2 የፖሊሲው ፍልስፍና፣ መርሆዎችና ዓላማዎች

### 3.2.1 የትምህርትና ሥልጠና ፍልስፍና

የኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና ፍልስፍና ከአገራዊ ፍላጎትና ተጨባጭ ሁኔታ የሚመነጭ እንደሁኔታውና እንደአግባቡ ባለብዙ ዘርፍ የትምህርትና ሥልጠና ፍልስፍና (Eclectic) የሚከተል ሲሆን ዋና ግብ ያደረገውም በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ፤ በራስ መተማመናቸው የዳበረ፤ ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ፤ ለራሳቸውና ለሀገራቸው ብልጽግና የሚተጉ በሁለንተናዊ መልኩ የዘመኑና ችግር ፈቺ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጎችን መፍጠር ነው።

### 3.2.2 የፖሊሲው መርሆዎች

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው አፈጻጸም የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት ያደርጋል፤

➢ **ጥራትና አግባብነት፤** ለሁሉም ዜጎች ጥራት ያለውና የሕይወት ዘመን ትምህርትና ሥልጠና ማቅረብ፣

➢ **ያልተማከለ አሠራር፤** ያልተማከለ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን መከተል፣

➢ **ግልጽነትና ምላሽ ሰጪ፤** ፖሊሲውና ስትራቴጂዎች ግልጽና ለችግሮች ምላሽ የሚሰጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

- **ከፖለቲካና ከሃይማኖት ነፃ፤** ትምህርትና ሥልጠና ከፖለቲካና ሃይማኖት ጣልቃገብነት ነፃ ሆኖ መስጠት፣
- **ውጤት ተኮር፤** የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የውጤት ተኮር ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን መከተል፣
- **ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ተወዳዳሪነት፤** የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ተወዳዳሪነትን መሠረት አድርጎ መተግበር፣

### 3.2.3 የፖሊሲው ዋና ዋና ዓላማዎች

- ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና በተለይም ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ነፃና የግዴታ ትምህርት በተስማሚ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለሁሉም በማዳረስ የግለሰብን አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ መንፈሣዊ እንዲሁም መልካም እሴቶችን ማጐልበት፣
- ትምህርትና ሥልጠናን ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሁም ከኢኮኖሚ ዘርፎች ለውጥና እድገት ጋር ማስተሳሰር፣
- በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የሀገረ-መንግሥት ግንባታን የሚያጠናክሩ እንዲሁም ሠላምን በዜጎች መካከል የሚያሰፍኑ እሴቶችን በማካተት ለሀገረ-መንግሥት ግንባታ የሚተጉ እንዲሁም የግብረገብነትና የሠላም እሴቶችን የተላበሱ ብቁ ዜጎችን ማፍራት፣
- ለነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡና ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚ ማልማትና ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ኢኮኖሚውን የሚያሳድጉ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጎችን ማፍራት፣
- የኢትዮጵያን መልካም ባህል የሚያበለጽጉ፤ ለሕዝብና ለሀገር ፍቅር ያላቸው፣ ብዙኃነትን የሚቀበሉ፣ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ፣ ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት፣ ለፍትሕ፣ ለሠላም ዘብ የሚቆሙ፣ በግብረገብ፣ በሥነ ምግባርና በዴሞክራሲ ባህል የታነጹ፣ የሀገራቸውን ታሪክ የሚያውቁ፣ ለሀገራቸው አንድነት ዘብ የሚቆሙ ሁለንተናዊ ሰብእናቸው የተሟላ ዜጎችን ማፍራት፣

- በራሳቸው የሚተማመኑ፣ እውነትን የሚሹ፣ ለእውነት የሚቆሙ፣ በምክንያታዊ ትንተናና በውይይት የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን የሚያፈልቁ፣ ውበትን የሚያደንቁ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ለሀገር በቀል እውቀት መስፋፋት፣ መስረጽና ማደግ የሚተጉ፤ በዚህም የመመራመርና የማመዛዘን ብቃታቸውን የሚያጐለብቱ እና ለሕግ ዘብ የሚቆሙ ዜጐችን ማፍራት፣
- ትምህርትና ሥልጠናን ለአካባቢው ተስማሚና ተገቢ በማድረግ አካባቢን የማወቅ፣ የማጤንና የመገንዘብ፣ የማመዛዘንና የመገምገም፣ የመተንተንና የመለወጥ እንዲሁም የማድነቅ ችሎታ ያላቸው ዜጐችን ማፍራት፣

## 4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች

የትምህርትና ሥልጠና ዘርፉን እየፈተኑ ያሉ እና ወደፊትም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ዋና ዋና ችግሮች እና ተግዳሮቶችን ለመፍታት እንዲሁም በሥራ ላይ ያለውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ክፍተቶችን ለመሙላት እና አዳዲስ እይታዎችን ለማካተት የሚከተሉት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮችና አቅጣጫዎች ተለይተዋል።

### 4.1 የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማዕቀፍ

- ከተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና ዘርፎችና ከሥራ ልምድ የሚገኙ ሙያዎች ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

### 4.2 የትምህርትና ሥልጠና እርከን

- የሀገሪቱን የትምህርት ዓላማዎች ለማሳካት እንዲቻል የትምህርት እርከን፤ አጠቃላይ ትምህርት ቅድመ አንደኛ ደረጃ (የ5 አመትና የ6 አመት ሕፃናት)፣ አንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍሎች)፤ መካከለኛ ደረጃ (7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች) እና ሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች) ይሆናል።
- እድሜያቸው አራት አመት የሞላቸው ሕፃናት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በሌሎች አማራጮች የሚማሩበት ሥርዓት ይዘረጋል።
- አንደኛ ክፍል የመግቢያ እድሜ 7 አመት ይሆናል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ስምንት ደረጃዎች (ከደረጃ 1- ደረጃ 8) ይኖሩታል።
- የከፍተኛ ትምህርት ቅድመ ምረቃ አነስተኛው 4 ዓመት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ 2 ዓመት እንዲሁም ፒ.ኤች.ዲ 4 ዓመት እንዲሆን ይደረጋል።
- በሁሉም የትምህርትና ሥልጠና ደረጃዎች ያልተማከለ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል።

## 4.3 የትምህርትና ሥልጠና ቋንቋ

- ተማሪዎች ቢያንስ ሶስት ቋንቋዎች እንዲማሩ ይደረጋል።
- የአፍ-መፍቻ ቋንቋ እንደትምህርት ዓይነትነት እና እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ የሚሰጥ ሆኖ በሁለቱም መሰጠቱ የሚያበቃበት የክፍል ደረጃ በክልሎች ተወስኖ ተግባራዊ ይደረጋል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ በትምህርት ዓይነትነት ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል፤ በማስተማሪያ ቋንቋነት ሥራ ላይ መዋል የሚጀምርበት በክልሎች የሚወሰን ሆኖ በአስገዳጅነት ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
- አንድ ተጨማሪ የሀገር ውስጥ ቋንቋ ከፌደራል የሥራ ቋንቋዎች መካከል የተማሪውን/የወላጅን ምርጫ ታሳቢ በማድረግ በየደረጃው ባለው የትምህርት መዋቅር ተወስኖ ከ3ኛ እስከ 10ኛ ክፍል የሚሰጥ ይሆናል።
- አንድ ተጨማሪ የውጭ ሀገር ቋንቋ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ አማራጭ ትምህርት የሚሰጥ ይሆናል።
- መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በእንግሊዝኛ የሚሰጥ ሲሆን አጫጭር እና ማህበረሰብ ተኮር ሥልጠናዎች እንደ ሠልጣኙ ፍላጎት በአገር ውስጥ ወይም በውጪ ቋንቋዎች ሊሰጥ ይችላል።

## 4.4 የነፃና የግዴታ ትምህርት

- መንግሥት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለ5 ዓመት እና ለ6 ዓመት ሕፃናት የሁለት አመት የነፃና የግዴታ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል።
- ሕፃናት በ7 ዓመታቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲጀምሩና ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ነፃና ግዴታ ሆኖ እንዲሰጥ ይደረጋል።
- የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ነፃና ግዴታ ሆኖ እንዲሰጥ ይደረጋል።
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች በነፃ እንዲሰጥ ይደረጋል።

## 4.5 የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት

### 4.5.1 አጠቃላይ ትምህርት

- የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ጥራት ባለው መልኩ የተቀረፀ የሀገር በቀል እውቀት፣ የሙያና የቀለም ትምህርትና የግብረገብ ትምህርት ያካተተና ከምርትና ከተግባር ጋር ተቀናጅቶ ብቃትን የሚያስጨብጥ ሥርዓተ-ትምህርት በማዘጋጀት በቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲሰጥ ይደረጋል።
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች በአጠቃላይ ትምህርት መልክ እንዲሁም በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍሎች በተለያዩ የትኩረት መስኮች ተደራጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።
- የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት ከሚያስተምሩበት የትምህርት ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት ጋር ተጣጥሞና ተገናዝቦ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲሰጥ ይደረጋል።
- ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ያላቸው፣ የአካል ጉዳተኝነትና ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች የሚያስተናግድ ሥርዓተ-ትምህርት ተዘጋጅቶ እንዲተገበር ይደረጋል።
- የሙያ እና ቴክኖሎጂ ትምህርት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ ከእድሜያቸው ጋር የተመጣጠነ ሆኖ እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የግብረገብ ትምህርት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍሎች ራሱን ችሎ፣ ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ በዜግነት ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የጎልማሶች ትምህርት የጎልማሳውን መሠረታዊ እና ሁለንተናዊ ሕይወቱን ለማሻሻል በሚያስችል መልኩ የትምህርትና ሥልጠና ተለማጭ ሆኖ እንዲሰጥ ይደረጋል።

- ሥርዓተ-ትምህርቱ በየጊዜው ጥናትን መሠረት አድርጎ እንዲሻሻል ይደረጋል።

## 4.5.2 የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሙያ ደረጃ የእሴት ሠንሰለት ትንተናን ተከትሎ ኢንዱስትሪውን፣ የሙያ ማህበራትን፣ የአሠሪ ማህበራትን፣ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችንና አሠልጣኞችን በማካተት እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርትና የሥልጠና መሣሪያዎች የሙያ ደረጃን መሠረት በማድረግ በማዕከል ተቀርጸው ተቋማት ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አስተሳስረውና አዛምደው ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ክለሳ የኢንዱስትሪ ሙያተኞችን አሠልጣኞችንና የሙያ ማህበራትን ያሳተፈ እንዲሆን ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት የሙያ የብቃት አሀዶችን፣ አጠቃላይ የብቃት አሀዶችንና የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶችን እና የሥራ ፈጣሪነትን ያካተተ እንዲሆን ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት የአካባቢ ጥበቃን የዘላቂ ልማትንና የሥራ ላይ ጤና እና ደህንነትን እንዲያካትት ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አማራጭ የትብብር ሥልጠና ሞዴሎችን በመጠቀም እንደየሙያው ዓይነት የሚለያይ ሆኖ ቢያንስ 70% ተግባር ተኮር እንዲሆንና በኢንዱስትሪና በማሠልጠኛ ተቋማት ትብብር እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለአጫጭር ሥልጠናዎች ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተለማጭ የሥልጠና ሥነ-ዘዴን እንዲከተል ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ካካበቱት ልምድ እና የተወዳዳሪነት ደረጃ ጋር የተጣጣመ፣ የተፈጥሮ ፀጋን፣ ተልዕኮ እና የትኩረት መስክን መሠረት ያደረገ የሥልጠና ፕሮግራሞች ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል።

- በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ሠልጣኞች በእያንዳንዱ የሙያ መስክ ጋር የተሳሰረ የሙያ ሥነ ምግባር ኮርስ እንዲሰጥ ይደረጋል።

### 4.5.3 የከፍተኛ ትምህርት

- በሀገሪቱ የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት መርሃ-ግብሮች ከሀገር እና ከዓለም አቀፍ ልማትና እድገት እንዲሁም ከሰው ኃይል ገበያ ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ጥራትና ተገቢነት ያላቸው የትምህርት መርሃ-ግብሮች ከሴክተሮችና ከኢንዱስትሪው ፍላጎት አንጻር እየታየ እንዲከፈቱ ይደረጋል።

- ሁሉም ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ቢያንስ ሀያ በመቶ የሚሆነውን ጊዜ በኢንዱስትሪ ወይም ከሚሠለጥኑበት የሙያ መስክ ጋር የተያያዘ የተግባር ትምህርት የሚያገኙበት አሠራር ይዘረጋል።

- በእያንዳንዱ የሙያ መስክ ከመርሃ ግብሩ ጋር የተሳሰረ የሙያ ሥነ ምግባር ኮርስ እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት መርሃ-ግብሮች ካካበቱት ልምድ እና የተወዳዳሪነት ደረጃ ጋር የተጣጣመ፣ የተፈጥሮ ፀጋን፣ ተልዕኮ እና የትኩረት መስክ (differentiation) ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል።

- የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ተወዳደሪነታቸውን ለማጎልበት ወደራስ ገዝነት የሚሸጋገሩበት ሥርዓት ይዘረጋል።

## 4.6 የመምህራን/አሠልጣኞችና የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት አመራሮች ደረጃ

- በየዘርፉና በየደረጃው የሚሰማሩ የመምህራን፣ የአሰልጣኞች እና የትምህርት አመራሮች የትምህርት ደረጃ ከሰርተፍኬት እስከ ዶክትሬት ዲግሪ እንዲሆን ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

- የመምህራን፣ የአሰልጣኞች እና የትምህርት አመራሮች ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር እንዲሁም የሙያ ፍቃድና እድሳት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይህም ከደረጃ እድገታቸው ጋር እንዲተሳሰር ይደረጋል።

## 4.7 የምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት

- በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር ተጣምረው የማህበረሰብን ለውጥ እንዲያመጡ በሚያስችል መልክ ተሳስረው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

- ዩኒቨርስቲዎች በጥናትና ምርምር፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በጉድኝት የሚገኙበትን አካባቢና የልማት ኮሪደር (cluster) ቅድሚያ ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል።

- የምርምርና የማህበረሰብ ጉድኝት ሥራዎች እንደተቋማቱ ተልዕኮ የሚወሰን ሆኖ ቢያንስ ተቋማት የበጀታቸውን 5% በመመደብ እንዲደግፉ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

- የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት መርሃ-ግብሮችን ከኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር ያጣጣመና ተወዳዳሪነቱንና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት፣ የዩኒቨርሲቲ፣ የምርምር ኢንስቲትዩትና ኢንዱስትሪ ትስስር እንዲኖር ይደረጋል።

## 4.8 የትምህርትና ሥልጠና ፋይናንስ

- ውጤታማ፣ ተጠያቂነትን ያሰፈነ እና ሚዛናዊ የሆነ ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ እንዲኖር ይደረጋል።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

- የከፍተኛ ትምህርት ወጪ በመንግሥትና በተማሪዎች የሚሸፈን ሆኖ በመንግሥት የሚሸፈነው ድርሻ እና በተማሪዎች የሚሸፈነው ድርሻ እንዲሁም ተማሪዎች የሚከፍሉበት ሥርዓት ዝርዝር በሕግ ይወሰናል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ለኢኮኖሚው ከሚያደርገው አስተዋጽኦ አንፃር በጥናት ላይ ተመሥርቶ በመንግሥት ተገቢው የበጀት ድጋፍ እንዲኖረው ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሠልጣኞች በወጪ መጋራት ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

- ኢንዱስትሪዎች/አሠሪዎች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ድጋፍ የሚያደርጉበት ሥርዓት ይዘረጋል።

- የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የውስጥ ገቢ በማመንጨት ወጪያቸውን የሚሸፍኑበት የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

- ሀገር አቀፍ የትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፈንድ ይቋቋማል።

## 4.9 የትምህርትና ሥልጠና ምዘና ሥርዓት

### 4.9.1 የአጠቃላይ ትምህርት

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ (6ኛ ክፍል) ፈተና በክልል ደረጃ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ (8ኛ ክፍል) ፈተና ትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው ስታንደርድ መሠረት ፈተናውን የማዘጋጀትና የማስተዳደር ሥራ በክልሎች እንዲከናወን ይደረጋል።

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ አገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ፈተና በቀለም እና በሙያ ትምህርት ትኩረት መስኮች በሁለት መልክ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

### 4.9.2 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

- 12ኛ ክፍል አጠናቀው ወደ ሥራው ዓለም መቀላቀል ለሚፈልጉ በ2ኛ ደረጃ መርጠው በተማሩት የሙያ ትምህርት መሠረት የብቃት ምዘና እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የብቃት ምዘና በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን ኢንዱስትሪው ምዘና ሊሰጥ በማይችልበት ሁኔታ የብቃት ምዘናው የክላስተር የምዘና ማዕከላትን፣ ተንቀሳቃሽ የምዘና ማዕከላትንና ሱሙሌሽን በመጠቀም እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የብቃት ምዘናው የአካል ጉዳተኞችንና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን አካታች እንዲሆን ይደረጋል።

- የኢንዱስትሪ መዛኞችን በዘላቂነት በምዘና ሂደቱ እንዲሳተፉ ብቃታቸውንና ሙያዊ ሥነ-ምግባራቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል የመዛኝነት ፈቃድ ዕውቅናና ዕድሳት (Licensing and Re-licensing) ሥርዓት ይዘረጋል።

- ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚደረገው ሽግግር በተቋም ውስጥ ምዘና የሚረጋገጥ ሲሆን በየትኛውም ደረጃ ወደሥራው አለም መግባት የሚፈልጉ ሠልጣኞች ብቻ አገራዊ የብቃት ምዘና የሚወስዱ ይሆናል።

### 4.9.3 የከፍተኛ ትምህርት

- በሁሉም የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ ግብሮች የመውጫ ፈተና እንዲሰጥ ይደረጋል።

- የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች ዓለም አቀፍ እውቅና (accreditation) ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

### 4.9.4 አነስተኛ የማለፊያ ወይም የመሸጋገሪያ ውጤት

- የተማሪዎች/የሠልጣኞች ከክፍል ወደ ክፍል ወይም ከደረጃ ወደ ደረጃ የሚደረገው ሽግግር አነስተኛው አማካይ ውጤት 50%ና በላይ ይሆናል፡፡

## 5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች

### 5.1 ፍትሃዊ፣ አካታችና ተደራሽ ትምህርትና ሥልጠና

ትምህርትና ሥልጠናን ፍትሀዊ፣ አካታችና ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀምና የግሉንም ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ ደረጃቸውን የጠበቁ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በመገንባትና በማስፋፋት፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ግብአት በማሟላት፣ በየደረጃው ለሚገኙ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አቅም በማሳደግ፣ አገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ በማድረግ፣ የትብብርና የቅንጅት የአሠራር ሥርዓት በማጠናከር፣ በበቂ በጀትና ማትጊያ የታገዘ እንዲሆን በማድረግ እና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ በማስቻል ፍትሀዊ፣ አካታችና ተደራሽ ትምህርትና ሥልጠና ይረጋገጣል።

### 5.2 በሥራ ገበያ ላይ ብቁና ተፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል

በሁሉም ደረጃዎች የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን በማረጋገጥ ሁሉም ተማሪዎችና ሠልጣኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጋቸውን እና ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት አሻሽሎ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት፣ በትምህርትና ሥልጠና ምዘና፣ በፈተናና ግምገማ ሥርዓት፣ በትምህርትና ሥልጠና ኢንስፔክሽን፣ የመምህራንና አሠልጣኞች እንዲሁም የአመራሮች ብቃት በምዘና በማረጋገጥ፣ የምርምር ሥራዎችን ጥራትና አግባብነትን በማሳደግ፣ ቋንቋዎችን በማበልፀግና የተማሪዎችንና የመምህራንን የቋንቋ አጠቃቀም በማሻሻል፣ የቤተ-ሙከራዎችን ግብአት በማሟላት፣ የተመራማሪዎችን የምርምር አቅም በማሳደግና ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ አገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ በማድረግ፣ የእርስ በርስ እና ዓለም አቀፍ ትብብርና ትስስርን በማጠናከር ጥራትና አግባብነቱ የተረጋገጠ ለሥራ ገበያው የሚመጥን የሰው ኃይል ይቀርባል።

### 5.3 ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና የሥራ ፈጠራ መስፋፋት

በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ፋይዳን በመረዳት ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ ለኢንተርፕራይዞች በማሸጋገር፣ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማድረግ እና የቴክኖሎጂ አቅም የመገንባት ሥራ በመሥራት፣ ቴክኖሎጂን በውል በመገንዘብና መቅዳት የሚያስችል አቅም በመገንባት፣ የአካባቢን ፀጋዎች መሠረት በማድረግ ትንተናዎችን በመሥራት፣

ቴክኖሎጂዎችን በመለየት፣ በማልማት፣ በማላመድ እና በማቀብ፣ በትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ ውስጥ የምርምር አቅም ሳይንሳዊ አካሄድን በአግባቡ ተከትሎ መፍትሔዎችን በማስቀመጥ፣ ተቋማቱ የአገር በቀል ዕውቀትና ክህሎትን በማዳበር፣ ፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማጎልበት፣ የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምህንድስናና ስነጥበብ ትምህርቶችን ልዩ ትኩረት በመስጠት በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት፣ ተማሪዎችና ሠልጣኞችን በማብቃት የአገር ኢኮኖሚን በማሳደግ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትምህርቶችንና የሙያ ሥልጠናዎችን ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ ተገቢ በሆነ መንገድ ብቁ መምህራንና አሠልጣኞች ለትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቤተ ሙከራዎች፣ ወርክሾፖችና ሌሎች ማቴሪያሎችን በመጠቀም ትምህርትና ሥልጠናውን በመስጠት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና የሥራ ፈጠራ ይስፋፋል።

## 5.4 የማህበረሰብና የአካባቢ ልማት

የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በማድረግ፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚደረግን የእውቀት እና ክህሎት ድጋፍ በማሳደግ፣ የበጎ አድራጎት አገልግሎትና የአካባቢ ልማትና ጥበቃን እንዲሁም ከአገር በቀል እውቀትና ክህሎት ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ፣ የተለያዩ አካባቢዎች ያላቸውን የልማት ጸጋዎች መሠረት ያደረገ የትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት፣ በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚከናወኑ የምርምርና ጥናት ሥራዎች የአካባቢውን ማህበረሰብ የልማት ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ የአካባቢው ማህበረሰብና ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ቀጣይነት ያለው አካባቢያዊ ልማት ይረጋገጣል።

## 5.5 ጠንካራ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እና የማስፈጸም አቅም

በዚህ ፖሊሲ እና በሌሎች የህግ ማዕቀፎች በመመስረት በትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የማስፈጸም አቅም በመገንባት፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ራስ ገዝ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የአገልግሎት ማሻሻያ ሥራዎችን በመሥራት፣ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት፣ የተቋማት መሠረተ ልማት ተደራሽነትን በማሳደግ ጠንካራ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እና የማስፈጸም አቅም ይገነባል።

## 6. ፖሊሲ የማውጣት ስልጣንና የፖሊሲው ወሰን

ይህ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በትምህርት ሚኒስቴር እና በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሀሳብ አመንጭነት ተዘጋጅቶና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል።

ይህ ፖሊሲ በአገሪቱ ባሉ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍሎች)፣ በመካከለኛ ደረጃ (7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች)፣ በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች)፣ በጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት (ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 8)፣ በትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች)፣ በትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና በኢንዱስትሪ ውስጥ በሚሰጡ ሥልጠናዎች (አጫጭርና መደበኛ ሥልጠናዎች) ተግባራዊ ይሆናል።

## 7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

### 7.1 የፖሊሲው ፈፃሚ አካላት

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት ዋና ዋና አስፈፃሚ አካላት ይኖሩታል።

- የሣይንስ፣ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀገር ደረጃ የሚካሄዱ የቴክኖሎጂ ምርምርና ጥናትን በማስተባበር፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ዲጂታላይዜሽን በማስፋፋት፣ የአይሲቲ መሠረተ ልማት በማስፋፋት፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ከትምህርትና ሥልጠናው ጋር በማስተሳሰር ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር እገዛ ያደርጋሉ። እንዲሁም በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በጥናትና ምርምር የሚመነጩ የቴክኖሎጂና ፈጠራ ሥራዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ።
- የማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሥራ ላይ ልምምድ ለሚያደርጉ ተማሪዎችና ሠልጣኞች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፣ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ዘመኑን የዋጀ የጤና፣ የባህል፣ የቱሪዝም፣ የሀገር በቀል፣ ወዘተ. እውቀትና ክህሎትን መሠረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት እንዲኖር እና የሙያ ስነ-ምግባር በአግባቡ በትምህርትና ሥልጠና ውስጥ እንዲካተት ያደርጋሉ። በትምህርትና ሥልጠና በጥቅም ላይ የሚውሉ ቋንቋዎች ለትምህርትና ሥልጠና ብቁ መሆናቸውን፣ ቋንቋዎች ለትምህርትና ሥልጠና እንዲውሉ ቋንቋዎችን የማልማት ሥራ

ይሠራሉ። ሕፃናት፣ ሴቶች እና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የትምህርትና ሥልጠና ተሳትፏቸውን የማሳደግ ሥራዎችን በመሥራት፣ ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች የትምህርትና ሥልጠና እድል እንዲያገኙ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይጠበቃል።

- የግብርና፣ የአምራች እና ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችን የሚመሩና የሚያስተባብሩ እንዲሁም የሚፈጽሙ ተቋማት በተለያዩ ዘርፎች ውስጥ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በተሰጣቸው ተልዕኮና የትኩረት መስክ መሠረት በማድረግ ተግባር ተኮር ትምህርትና ልምምድ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ።

- የፌደራልና የክልል የትምህርትና ሥልጠና ጥራት አረጋጋጭ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች በፖሊሲው ውስጥ የትምህርትን ጥራት፣ ደረጃ፣ የሙያ ደረጃ፣ ሙያዊ ስነምግባር እና ሌሎች የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎችን ያከናውናሉ።

## 7.2 ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች

የዚህን ፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች ለመፈፀም በተግባር ላይ ያሉት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አዋጅ፣ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ፣ የትምህርትና ሥልጠና የወጪ መጋራት ደንብ፣ በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የገቢ ማስገኛ የኢንተርፕራይዞች ደንብ፣ የዩኒቨርሲቲዎች ማቋቋሚያ ደንብ እና ሌሎች በሥራ ላይ ያሉ አዋጅና ደንቦች እንደአስፈላጊነቱ ተሻሽለው፣ እንዲሁም የአገር አቀፍ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማእቀፍ፣ የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ፣ የዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ አስተዳደር አዋጅ እና ሌሎች አስፈላጊ አዋጆችና ደንቦች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## 7.3 የፖሊሲው ማስፈጸሚያ ፕሮግራሞች

ፍትሃዊ፣ አካታችና ተደራሽ የሆነ ትምህርትና ሥልጠና ለማረጋገጥ፦ የትምህርት መሠረተ ልማት እና ፋሲሊቲዎችን ለመዘርጋት የትምህርትና ሥልጠና መሠረተ ልማትና ፋሲሊቲ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ይህ ፕሮግራም በዋናነት በሁሉም የትምህርት እርከኖች የትምህርት መሠረተ ልማቶችን እና የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች በተሟላ ሁኔታ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ፋሲሊቲዎችን ማሟላትና ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢ ሁኔታ መፍጠርን ያካትታል። በተጨማሪም ከመማር ማስተማር ባለፈ ለጥናትና ምርምር፣ ለማህበረሰብ

አገልግሎት እና ለትምህርትና ሥልጠና ኢንዱስትሪ ትስስር የሚከናወኑ መሠረተ ልማቶችንና ፋሲሊቲዎችን ያካትታል።

**በሥራ ገበያ ላይ ብቁና ተፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል ለማፍራት፦** የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ፣ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል። ይህ ፕሮግራም በዋናነት የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርትን ለማሻሻል፣ መምህራንንና የትምህርት አመራር ብቃት ለማሻሻል፣ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞችን ለማሻሻል፣ የአጠቃላይ ትምህርት ብሔራዊ ስታንደርድ ለማሻሻል፣ የቋንቋ ክህሎትን ለማሻሻልና ለማበልፀግ፣ የሕይወት ዘመን የጎልማሶች ትምህርት ለማሻሻል፣ የከፍተኛ ትምህርት መምህራንንና የትምህርት አመራር ብቃት ለማሻሻል፣ የዩኒቨርስቲዎች የተልእኮና የትኩረት መስክ ለማሻሻል፣ የምርምር ሥራዎችን ለማሻሻል፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ደረጃና ሥርዓተ ሥልጠና ዝግጅትና ክለሳ ለማድረግ፣ የአሠልጣኞችና አመራሮች ብቃት ለማሻሻል እንዲሁም የብቃት ምዘና ሥርአት ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያካትታል።

**ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና የሥራ ፈጠራን ለማስፋፋት፦** የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማሻሻያ ፕሮግራም የሚተገበር ይሆናል። ይህን ፕሮግራም ለማሳካት የኢንኩቤሽን ማእከላት ማስፋፋት፣ የቴክኖሎጂ ምርምር እና ሽግግር ማሻሻል፣ የውጪ አገር ሥራ ስምሪት ሥልጠና፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር ማሻሻል፣ የኢንተርፕራይዝ ልማት ማስፋፋት (enterprise development) የሚከናወኑ ይሆናል።

**የማህበረሰብና የአካባቢ ልማት ለማስፋፋት፦** የማህበረሰብ አገልግሎት እና አካባቢ ልማት ፕሮግራም የሚከናወን ይሆናል። ለዚህም የአገር በቀል እውቀትና ክህሎት ማሻሻያና ማሸጋገሪያ እና የልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማሻሻያ ጋር የተያያዙ ሥራዎች በዚህ ፕሮግራም ተፈፃሚ ይደረጋሉ።

**ጠንካራ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እና የማስፈጸም አቅም መፍጠር፦** የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የአቅም ግንባታና ተወዳዳሪነት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ራስ ገዝ፣ የአገልግሎት ማሻሻያ፣ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ እና የተቋማት መሠረተ ልማት አቅም ማሳደግ ጋር የተያያዙ ሥራዎች በዚህ ፕሮግራም ተፈፃሚ ይደረጋሉ።

## 7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈጻጸም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው አተገባበር ዘርፉ ለአገሪቱ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል ከማቅረብ፣ ጥራት ያለው፣ አካታችና ተወዳዳሪ የሆነ የትምህርት እና ሥልጠና ከማዳረስ፣ ሥራ እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ የሚያበረታታ እንዲሁም የማህበረሰብ ልማትን የሚያግዝና አካባቢያዊ ልማትን ከማፋጠን አንፃር የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል። የክትትልና ድጋፍ ሥራው ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ የማስፈፀሚያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ይህም የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች ለማሳካትና መሳካታቸውንና ወቅታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የፖሊሲ ክለሳ ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ለማረጋገጥ ያስችላል። በአጠቃላይ ይህን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ለመተግበር የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- በፌደራል፣ በክልል፣ በትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና በሌሎችም የዘርፉ መዋቅሮች መካከል ቅንጅታዊ አሠራርን የተከተለና ወጥ በሆነ መልኩ እንዲተገበር የሚያስችል ሁሉም አካላት የተሳተፉበት የድጋፍና ክትትል ስታንዳርድና የአፈፃፀም አመላካቾችን ያካተተ እና ከዓለም አቀፋዊ የግምገማ አመልካቾች አንጻር የተቃኘ ሰነድ ይዘጋጃል።
- በዘርፉ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፤ ይህን ለመፈጸም የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤ በሠለጠነ የሰው ኃይል የተሟላ ጠንካራ አደረጃጀት እንዲኖር ይደረጋል።
- በየሦስት ዓመቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት በመካከለኛ ዘመን ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ ሥራዎች መሻሻል በግብዓትነት እንዲውሉ ይደረጋል። ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት በትምህርትና ሥልጠና ባለድርሻ አካላትና ማህበረሰቦችን አካታች በሆነ መረጃ የማሰባሰብ ዘዴ እንዲሁም በተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መሠረት አድርጎ ይከናወናል።
- የትምህርትና ሥልጠናን ዓመታዊ አፈፃፀም ለመገምገም ከትምህርት ቤት እስከ ሀገር አቀፍ ድረስ የትምህርትና ሥልጠና ጉባኤ የሚካሄድበት ሥርዓት ይዘረጋል።

➢ ፖሊሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥናት ላይ ተመሥርቶ የአገርና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል።

## 8. ተዛማጅ ፖሊሲዎች

በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተለዩ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው።

### 8.1 የአምራች ዘርፎች እና የመሠረተ ልማት ፖሊሲዎች

የግብርናና ገጠር ልማት የሥርዓተ-ምግብ እና የምግብ ደህንነት በማረጋገጥ ለጤና ጠንቅ እንዳይሆኑ እና በጤና እንከን ምክንያት የትምህርት ብክነት እንዳይከሰት እንዲሁም ተማሪዎች በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያደርግ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ የትምህርት እና ኢንዱስትሪዎች ትስስር እንዲኖር ለማድረግ እና የትምህርትና ሥልጠና የሰው ሀብት ልማት ከኢንዱስትሪዎች የተማረ የሰው ሀይል እና ክህሎት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል። የውሀ ልማት ፖሊሲ በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ደረጃ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ የንጽሕና አጠባበቅ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ከማስፋፋት አንፃር የበኩሉን የሚወጣ ይሆናል። የኤሌክትሪክ ፖሊሲ በየደረጃው ያሉ የትምህርት ተቋማት የኤሌክትሪክ እና ሌሎች የሀይል አማራጭ አቅርቦት እንዲሟላላቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው ሲሆን የኮንስትራክሽን ፖሊሲ የመሠረተ ልማት ግንባታ የዲዛይን እና ደረጃ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ ድጋፍ በማድረግ በሁሉም ደረጃ ያሉ የትምህርት ተቋማት ወጥ የመሠረተ ልማት እንዲኖራቸው ያግዛል።

### 8.2 የማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች

የጤና ዘርፍ ፖሊሲ የዜጎችን ጤንነት በማሻሻል እና የእናቶች እና የህጻናት ህክምና አገልግሎት በማሻሻል፣ የሥርዓተ ምግብ፣ በሽታዎች በመከላከልና መቆጣጠር እንዲሁም የግል ንጽሕናና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ በማሻሻል ሁሉም ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ህጻን ትምህርት እንዲያገኝ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን የመጠለያ፣ የምግብ፣ የመድህኒትና ሌሎች የህክምና አግልግሎቶች፣ የትምህርት ተቋማት እንዲያገኙ ያደርጋል። የሴቶች ፖሊሲ ከትምህርት ጋር የተሳሰሩ ሥልጠና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም እናቶች ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ የማስተማር

ኃላፊነት ይኖረዋል። የወጣቶች ፖሊሲ ወጣቶችን የትምህርት ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው የሚችለውን የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን፣ የሥነልቦና አገልግሎቶችን በመስጠት አስተዋጽኦ የሚኖረው ሲሆን የህጻናት ፖሊሲ ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ፣ መሠረታዊ የህፃናት የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ እና ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት የጤና አገልግሎት፤ የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚከናወኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ከመስራት እና በአጠቃላይ አመለካከትን እና ባህልን ከማጎልበት አንፃር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። የስፖርት ፖሊሲ ማህበረሰቡን በማስተባበር የአካል እንቅስቃሴ እንዲደርግ በማድረግ በአካልና በአምሮ የዳበረ ዜጋ በማፍራት ለትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የባህል ፖሊሲ የትምህርትና ሥልጠና ውጤታማ እንዳይሆኑ ጐታች ልማዳዊ ድርጊቶች እንደ ያለ እድሜ ጋብቻ የመሳሰሉ ተግባራት እንዲወገዱ የማድረግ ኃላፊነት፣ ማህበረ-ባህላዊ ተቋማት እንዲጠናከሩና ተፅዕኖ እንዲፈጥሩ የማገዝ ኃላፊነት ይወጣል፣ የፊልም ፖሊሲ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ፣ በሀገር ደረጃ የሚታዩ ፊልሞች የሀገሪቱን እሴቶች የጠበቁ እንዲሆን በማድረግ አላስፈላጊ የሆኑ የባዕዳን ሀገር ድርጊቶች በትምህርት ላይ የሚደርሱ ችግሮች እንዲወገዱ ያደርጋል።

## 8.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምርን በመደገፍ የትምህርትና ሥልጠና መሣሪያዎች፣ የግብዓት አቅርቦት እንዲሻሻል ማገዝ፣ በትምህርት ተቋማት ሚከናወኑ የሳይንስ፣ ጥናትና ምርምር እና ፈጠራ ሥራዎች ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ የሳይንስ፣ የቴእክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን መሠረተ ልማቶች በተገቢ ሁኔታ እንዲቀርቡ ማድረግ፣ የትምህርት መረጃ አስተዳደር በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመደገፍና በማዘመን የትምህርት ጥራት ለሁሉም እንዲዳረስ የማድረግ እና በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚሰሩ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል። የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የትምህርት ግብዓቶችና መሣሪያዎች ደረጃዎችን በማስጠበቅና ማረጋገጥ ሚና ይኖረዋል።

## 8.4 የፍትህና የአስተዳደር ፖሊሲዎች

የሠላም ፖሊሰ በትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሠላም መሰረተ ልማት እንዲዘረጉ በማድረግ ክበባትና ፎረሞች እንዲቋቋሙ፣ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ወይም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

እንዲዘረጉ በጋራ በመሥራት፣ ሥልጠናዎችን በዩኒቨርሲቲዎች ቅንጅት እንዲሰጥ በማድረግ፣ የዜጎችን አካላዊ፣ አእምሮዊ እና አካባቢያዊ ነፃነትና ደህንነት በማስጠበቅ፣ ሰላማዊና ፍትሃዊ አስተሳሰብ እና አሠራርን በማረጋገጥ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ያለምንም የሠላም ችግር ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል። የሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ ለትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ውጤታማነት አደረጃጀትና አሠራር እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ እና የትምህርት ዘርፍ ባለሙያዎች የሚያበረታታ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለትምህርት ዘርፍ ኢንቨስትመንት መሳብ እና ከልማት አጋሮች የትምህርት ፋይናንስ ማሰባሰብን ማገዝ ላይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

## 9. መሠረታዊ የቃላት ፍቺ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ውስጥ፤

- **የትምህርትና ሥልጠና ፍልስፍና** ማለት የሀገሪቱ ትምህርትና ሥልጠና የሚመራበትን መሠረትና አቅጣጫ የሚያሳይ ነው።
- **ስትራቴጂ** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚያገለግል ስልት ነው።
- **መርህ** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን ለማስፈፀም የምንከተለው መሠረታዊ መመሪያ ነው።
- **የትምህርትና ሥልጠና እርከን** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ዓላማን ለማሳካት የተቀረፀው ሥርዓተ-ትምህርት የሚከፋፈልበት ደረጃ ነው።
- **ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት** ማለት ከ4 ዓመት እስከ 6 ዓመት ያሉ ሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት በማጐልበት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚደረጉበትና መሠረት የሚጣልበት የትምህርት ደረጃ ነው።
- **አንደኛ ደረጃ ትምህርት** ማለት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ደረጃዎችን የሚያካትት ሆኖ ሕፃናት የማንበብ፤ የማስላት፡ አካባቢን የማወቅና መጠበቅ፣ ወዘተ. መሠረታዊ እውቀቶች፣ ክህሎት የሚጨብጡበትና የሚያዳብሩበት መልካም የግብረገብነት ባህሪ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የሚሳበሱበት የመሠረታዊ ትምህርት አካል ሆኖ የሚሰጥበት የትምህርት መርሃ-ግብር ነው።

- **መካከለኛ ደረጃ ትምህርት** ማለት ተማሪዎችን የ7ኛና 8ኛ ክፍል ትምህርት በማስተማር ለቀጣይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽግግር ዝግጁ የሚሆኑበት የትምህርት ደረጃ ነው።

- **ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት** ማለት ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያሉትን ክፍሎች የሚያጠቃልል ሲሆን የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ትምህርት በመካከለኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት እየተጠናከረ የሚቀጥልበት እንዲሁም የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ትምህርት በተለያዩ የትኩረት መስኮች ተከፍሎ ተማሪዎችን ለከፍተኛ ትምህርትና ለሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያደርግ የትምህርት ደረጃ ነው።

- **የጎልማሶች ትምህርት** ማለት ይዘቱና የትምህርት አሰጣጡ ዘዴ መደበኛ በሆነው ወይም ባልሆነው መንገድ ቢሆንም ጎልማሶች ችሎታቸውን ለማዳበር፣ ዕውቀታቸውን ለማበልጸግ ወይም የቴክኒክና የሙያ ብቃታቸውን ለማጎልበት በታቀደ መርሃ-ግብር በመደበኛ፣ በማታና በርቀት የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ የሚያልፉበት የትምህርት አሰጣጥና አቀባበል ሂደት ነው።

- **አጠቃላይ ትምህርት** ማለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ፤ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መርሀ ግብር ሲሆን፤ የጎልማሶች ትምህርትንም ያካትታል።

- **የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና** ማለት በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በተለያዩ የሙያ ዓይነቶችና ከሁለተኛ ደረጃ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ባሉ ደረጃዎች ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት እውቀትን፣ ክህሎትንና የሙያ ሥነ ምግባርን በማጎልበት እና በሙያ ብቃት ምዘና በማረጋገጥ ለሥራ ዝግጁ የሚደረግበት የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ነው።

- **የሙያ ደረጃ** ማለት በሥራ ዓለም በሚገኙ ሙያተኞች የሚዘጋጅ የሙያ ደረጃ ሲሆን ሰዎች በሥራ ዓለም ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ሊኖራቸው የሚገባውን ብቃት የሚያመለክት ነው።

- **ተለማጭ** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለተለዋዋጭ የሙያ መስፈርቶች ምላሽ የመስጠት እና በዓይነትና በመጠን ልዩነት ያላቸው ቡድኖችን የተለያዩ ፍላጎቶች የማስተናገድ ችሎታ ማለት ነው።

- **የአጭር ጊዜ ሥልጠና** ማለት ሠልጣኞች በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ለሥራ ብቁ እንዲሆኑ፣ የደረጃ እድገት እንዲያገኙ ወይም በልዩ ሙያ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ሙያ ደረጃን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅና በአንድ ደረጃ ውስጥ ከሚሰጡ የብቃት አሃዶች ውስጥ የተወሰኑትን የያዘና ለአጭር ጊዜ የሚሰጥ ሥልጠና ነው።

- **የተቋም ውስጥ ምዘና** ማለት ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለደረጃው አጠናቃቂዎች ከአንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ከማለፋቸው በፊት በተቋም ደረጃ በራሳቸው በተቋማት የሚሰጥ የብቃት ምዘና ነው።

- **የሙያ ብቃት ምዘና** ማለት የሙያ ደረጃን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅና የተመዛኙን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በመለካት ለሥራው አለም ብቁ መሆኑን የማረጋገጥ ሂደት ነው።

- **ውጤትን መሠረት ያደረገ ምዘና** ማለት የሙያ ብቃቱ እንዴት፣ መቼና የት እንደተገኘ ግምት ውስጥ ሳይገባ የሙያ ብቃቱ ስለመኖሩ ብቻ የሚመዘንበት አሠራር ነው።

- **የትብብር ሥልጠና** ማለት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በሚሰጡ ተቋማትና ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ባላቸው ኢንዱስትሪዎች ወይም ኢንተርፕራይዞች ውስጥ የሚሰጥ በተግባር የተደገፈ ሥልጠናን የሚያካትት የሥልጠና ሥርዓት ነው።

- **ቴክኖሎጂ** ማለት ግብዓቶችንና ማሽነሪዎችን በመጠቀም አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልግ የቴክኒክ፣ የሥራ አመራር፣ የግብይት ዕውቀትና ችሎታ፣ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የአሠራር ሥርዓት እና የሥራ ባህልን መረዳት የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት ነው።

- **ቴክኖሎጂ ሽግግር** ማለት የሳይንሳዊና የቴክኖሎጂ ዕድገትን ለማረጋገጥ ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ ቴክኖሎጂን፣ የማምረቻ ዘዴን፣ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ናሙናዎችን



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ከአመንጪው ወደ ተጠቃሚው የማስተላለፍ ሂደት እና ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ መሥራትና ወደ አዳዲስ አሠራር ማሻሻል ማለት ነው።

- **ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ** ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን እንዲሁም የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በፍላጎት ላይ ተመሥርቶ በመለየት የተሟላ መረጃ ማደራጀት፣ ሥልጠናና ምክር መስጠት፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት እና ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን የሚያካትት ድጋፍ ነው።

- **አገር በቀል ዕውቀትና ክህሎት** ማለት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለረጅም ጊዜያት የኖሩ ልዩ የሆኑ የሙያ ዕውቀትና ክህሎቶች፣ ማህበረሰቡ የሚገለገልባቸው ሆነው መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚተላለፉ፣ መረጃዎች ከጽሑፎች ይልቅ በአፍ ወግ የሚነገሩና ጽሑፍ ላይ ያልሰፈሩ ማለት ነው።

- **አጠቃላይ ወይም ደጋፊ የብቃት አሃዶች** ማለት ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሠልጣኞች ዋናውን ሥልጠና የሚደግፉ ደጋፊ የብቃት አሃዶች ማለት ነው።

- **ከፍተኛ ትምህርት** ማለት ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ የቀለምና የሙያ እውቀት፣ ክህሎት፣ ሥነ ምግባር እና ብቃት በላቀ ሁኔታ እንዲጎለብት የሚያደርጉ የቅድመ ምረቃ እና የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብሮችን የያዘ የትምህርት ደረጃ ነው።

- **የትምህርትና ሥልጠና አመራር** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲን በሚጠበቀው መልኩ እንዲተገበር የተደራጀው የትምህርትና ሥልጠና መዋቅር ግብዓትንና ሂደትን በማቀናጀት ተገቢውን ውጤት እንዲያስገኙ በየደረጃው አመራር የሚሰጥ አካል ነው።

- **የትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር** ማለት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲን በየደረጃው ያሉት የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ተገቢውን የሰው፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ሀብት በማቀናጀት የዕለት-ተዕለት ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የሚደራጅ የአሠራር ሥርዓት ነው።

የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education